# ፍትሃዊ ተገቢና ተመጣጣኝ እርምጃ

## ክፍል ሁለት

*አዲስ ቶልቻ 08/17/13*

*በመንግስት በኩል የፌደራል ጉዳዮች ሚነስቴር "የሙስሊሙ ተወካይ ነን" ባሉ ወገኖች እንደችግር ለቀረበው አቤቱታ ምላሽ ለመስጠት አቤቱታ አቅራቢዎች ጋር ውይይት አካሄደ፡፡ በውይይቱ ላይ የእስልምና ምክር ቤት አባላትን ምርጫ በተመለከተ ጥያቄው ተገቢ መሆኑን የገለጹት የፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ባለስልጣናት፣ ሆኖም ጉዳዩ የሙስሊሙ ሕብረተሰብ በመሆኑ መንግስት ጸጥታን ማስከበርና መሰል ድጋፎችን ከማድረግ ያለፈ በጉዳዩ ውስጥ ጣልቃ የመግባት ስልጣን እንደሌለው አስታውቀ፡፡በዚሁ የምክር ቤቱ ምርጫ እንዲካሄድ መግባባት ላይ ተደረሰ፡፡*

*ይሄኔ አወሊያ መስጊድ ውስጥ እርስ በርስ ተመራርጠው "የሙስሊሙ ተወካይ" ነን ያሉት ግለሰቦች፣ በስራ ላይ በነበረው የእስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ላይ እምነት ስላልነበራቸው፣ ምርጫውን በገለልተኝነት እንዲካሄድ አያደርግም የሚል አቋም ይይዛሉ፡፡ በዚሁ መሰረት ገለልተኛ የሆነው አካል የእስልምና ሃይማኖት ሊቃውንት (ኡላማዎች) ጉባኤ በመሆኑ ምርጫውን እንዲያስፈጽም መግባባት ላይ ይደረሳል፡፡*

*የኡላማዎች ጉባኤ ለወራት ያህል ዝግጅት ሲያደርግ ከቆየ በኋላ በ2005 ዓ/ም መስከረም ወር ላይ የእስልምና ጉዳዮች ምክር ቤት አባላት ምርጫ ተካሄደ፡፡ በምርጫው ላይ 8 ሚሊየን ያህል ለአካለ መጠን የደረሱ ሙስሊሞች ተሳትፈዋል፡፡ የምርጫው አካሄድ በግልጽ የድምጽ አሰጣጥ ስርአት በዚሁ አኳሆን በተመረጡ አስመራጮች አማካኝነት የተካሄደና ውጤቱ እዛው የታወቀ በመሆኑ ተአማኒነቱ አጠራጣሪ አልነበረም፡፡*

*በዚህ አኳኋን በቀበሌ ደረጃ የተመረጡት የሙስሊሙ ተወካዮች ተሰብስበው የወረዳ፣ የዞንና የክልል በመጫረሻም ከየክልሉ ተመርጠው የተወከሉት ክልላዊ የእስልምና ጉዳዮች ምክር ቤት አባላት አገራዊ የእስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት አባላትንና አመራሮችን ሰይመው አዲሱ መጅሊስ በይፋ ስራውን ጀመረ፡፡ በዚህ አኳኋን ተሰይሞ ስራውን የጀመረው መጅሊስ እነሆ አንድ አመት ሊሞላው ወራት ቀርተውታል፡፡*

*እንግዲህ ከ1 ሺህ እስከ 1 ሺህ 500 የሚሆኑ ግለሰቦች አወሊያ መስጊድ ውስጥ ተሰብስበው የመረጡዋቸው 17 ያህል ግለሰቦች ደጋፊዎች በየአጋጣሚው "የሙስሊሙ ተወካዮች" ሲባሉ*

ይደመጣል፡፡ የሙስሊሙ ተወካዮች ግን በይፋ 8 ሚሊየን ለአካለ መጠን የደረሱ ሙስሊሞች በግልጽ የድምጽ አሰጣጥ ስርአት የመረጡዋቸው በየደረጃው ያሉ የመጅሊስ አባላት ናቸው፡፡ 17ቱን ግለሰቦች " የሙስሊሙ ተወካዮች" እያሉ የሚጠሩዋቸው የከሸፈ ሃይማኖትን ሽፋን ያደረገ የፖለቲካ አጀንዳቸው ሕይወት እንዲዘራ ነው፡፡

ቡድኑ በሁለተኛ ደረጃ ያነሳው ጥያቄ "አሕባሽ" የተሰኘው የእስልምና ሃይማኖት አስተምህሮ መስጠት ይቁም የሚል ነው፡፡ የፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር በዚህ ጉዳይ ላይ በሰጠው ምላሽ፣ ምን አይነት አስተምህሮ መቼና በማን መሰጠት አለበት የሚለውን መወሰን የመንግስት ጉዳይ ሳይሆን የእስልምና ሃይማኖት የበላይ መሪ የሆነው የመጅሊሱ ስልጣን መሆኑን አሳውቋል፡፡ ከዚሁ ጋር አያይዞ ማንኛውም ዜጋ የፈቀደወን ሃይማኖትና እምነት የመከተል ሕገመንግስታዊ መብት ስላለው ይህን መከልከል አይቻልም አሳውቋል፡፡ እርግጥ ሰበካው በግዳጅ እይተሰጠ ከሆነ ይህ ተገቢ ባለመሆኑ እንዲጣራ መገባባት ላይ ይደረሳል፡፡

አህባሽ የሚል ስያሜ የተሰጠውንና  የአወሊያው ቡድን "ከአገር ይጥፋልኝ" ያለውን አስተምህሮ ጉዳይ እንዲያጣራ በጉዳዩ ላይ ጥልቅ እውቀት ያላቸው  የእስልምና ሊቃውንት (ኡላማዎች) ጉባኤ ሃላፊነት ተሰጠው፡፡ የኡላማዎቹ ጉባኤ ማጣራቱን አከናውኖ አንድም ቦታ በግዳጅ የሚሰጥ ሰበካ አለመኖሩ፣ አሕባሽ የተባለ አዲስ አስተምህሮ መጣብን የተባለውንም በተመለከተ ኢትዮጵያ ውስጥ ከሺህ አመታት በላይ ሲሰበክ ከቆየው ከአሕለል ሱና አስተምህሮ የተለየ አንዳችም የተለየ አስተምህሮ እንዳልተሰጠ በይፋ ምስክርነት ሰጠ፡፡

ይሁን እንጂ አወሊያ መስጊድ ውስጥ ተመራርጠው ራሳቸውን "የሙስሊሙ ተወካይ" ብለው የሰየሙት ግለሰቦችና የቀፈቀፉዋቸው ከኢትየጵያ ሙስሊም ሕብረተሰብ ጋር ሲወዳደሩ እጅግ አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ጀሌዎቻቸው የኡላማዎች ጉባኤ የሰጠውን ምስክርነት ሊቀበሉ አልፈቀዱም፡፡

ቡድኑ አንስቶት የነበረው ሶስተኛ ጥያቄ "አወሊያ ተቋም የሙስሊሙ ተቋም ስለሆነ ለሙስሊሙ ይመለስ" የሚል ነበር፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ በተደረገ ውይይት እርግጥም ተቋሙ የሙስሊሙ ሕብረተሰብ መሆኑ መግባባት ላይ ተደርሷል፡፡ ተቋሙ የሙስሊሙ በመሆኑ የኢትዮጵያ እስልምና ሃይማኖትን በበላይነት ለመምራት በሙስሊሙ ውክልና በተሰጠው የእስልምና ጉዳዮች ምክር ቤት ስር ሆኖ ሕዝብ የወከላቸው አባላት በተካተቱበት ቦርድ እንዲተዳደር ስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡አሁን ተቋሙ በዚህ አኳኋን እየተዳደረ ይገኛል፡፡ አንድን ሃይማኖታዊ ተቋም ሁሉም

የባለቤትነት ስሜት እንዲሰማውና ፍትሃዊ ጥቅም እንዲያገኝ ለማስቻል ከዚህ የተሻለ አንዳችም አስተዳደራዊ አማራጭ የለም፡፡

ይህ ሁኔታ መንግስት "የሙስሊሙ ሕብረተሰብ ችግሮች ናቸው" ተብለው የተነሱትን ጉዳዮች በውይይት በሰላማዊ መንገድ እልባት እንዲያገኙ ማድረጉን ያረጋግጣል፡፡ አንድነት በመግለጫው መንግስት የሙስሊሙ ችግሮች ተብለው ለቀረቡት ጥያቄዎች መፍትሄ ለማበጀት ምንም ያደረገው ሰላማዊ ጥረት የሌለ አስመስሎ " ሙስሊሞች ያነሱዋቸውን ጥያቄዎች በአስተውሎት በማየት፣ እንዲሁም ወደ ውይይት በመምጣት ፍጹም ሰላማዊ በሆነ መንግድ ምላሽ እንዲሰጥ ሳሳስብ ቆይቻለሁ" ሲል ተቆርቋሪ መስሎ ለመቅረብ ሞክሯል፡፡

እዚህ ላይ እኛ ሰላም ወዳድ ኢትዮጵያውያን የምናስታውሰው አንድነት የሙስሊሞች ጥያቄ በሚል የቀረቡት ጉዳዮች ሰላማዊ እልባት እንዲያገኙ ሲያሳስብ ሳይሆን፣ ወደ አመጽ እንዲገቡ ሲያበረታታና አደባባይ ወጥተው አሳፋሪና ሕግውጥ ድርጊቶቻቸውን እንደ ጀብድ ቆጥረው እንዲሸልሉ ማድረጉን ነው፡፡ አንድነት በደሴ ጠርቶት የነበረውን ሰላማዊ ሰልፍ ለዚህ አስረጂነት መጥቀስ ይቻላል፡፡

አንድነት በደሴ በጠራው ሰላማዊ ሰልፍ ላይ ወጥተው ሕገወጥ ድንፋታዎችን በማስተጋባት ሰልፉን ያሞቁለት በአካባባው የተስፋፋው የአክራሪነት አመለካከት ውጤት የሆኑ ጀብደኛ ጎሮምሶች ናቸው፡፡ አክራሪነት ባልተስፋፋባቸው ጎንደር፣ አርባምንጭ፣ በወላይታ ሶዶና ጂንካ ከተሞች በጠራቸው ሰላማዊ ሰልፎች ላይ የተገኘው ሕዝብ ከሃምሳ የማይበልጥ መሆኑ ለዚህ አስረጂነት ሊጠቀስ ይችላል፡፡

እንግዲህ አንድነት አክራሪዎቹ በሕዝብ የተተፉ አጀንዳቸውን አደባባይ ይዘው የሚወጡበት እድል ስለሰጣቸው በዚህ የልብ ልብ ተሰምቷቸዋል፡፡ እናም በሮመዳን ወር ጾም በተለይ በአዲስ አበባ ሁሉም ሙስሊም በሚታደምባቸው የአርብ የጸሎት ስርአቶች ላይ ሁከቶች ለማካሄድ ተዳፈረዋል፡፡ በእነዚህ ሁከቶች በሰላም ሃይማኖታቸው የሚያዛቸውን የጸሎት ስርአት ለመከወን የወጡ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ሙስሊሞች ጸሎታቸው ተረብሿል፤ ተሸማቀዋል፡፡

የዋሃቢ ሰለፊ የአክራሪነት እንቅስቃሴ ውስጥ ለውስጥ በተካሄደባቸው ያለፉ ጥቂት አመታት በኢትዮጵያ ለዘመናት የኖረው የእስልምና ሃይማኖት ስርአት የሚተገበርባቸው በርካታ መስጊዶች ተቃጥለዋል፡፡ እስልምናን በኢትዮጵያ በማስፋፋትና በማስተማር ስራቸው የሚዘከሩ ታላላቅ

የሃይማኖት አባቶችና መሪዎች መቃብሮች ተቆፍረው አጽማቸ ወጥቶ ተቃጥሏል፡፡ በሕይወት ያሉ የሃይማኖት አባቶችና መሪዎቸ ተደብድበዋል ተገድለዋል፡፡

አንድነት በጠራው ሰላማዊ ሰልፍ ላይ በሼህ ኑሩ ላይ የተፈጸመውን አሰቃቂ ግድያ "ድራማ ነው" እያስባለ ሲያላግጥ እንደነበረ ተመልክተናል፤ ሰምተናል፡፡ አንድነት እርግጥ ለሙስሊሞች መብት የሚቆረቆር ቢሆን ኖሮ አክራሪው ወገን በሰላማዊ ሙስሊሞች ላይ የፈጸመውን አስከፊ የመብት ጥሰት ያወግዝ ነበር፡፡ አንዴም ይህን አድርጎ አያውቅም፡፡

እንግዲህ አንድነት ነሃሴ 2፣ 2005 ዓ/ም በአዲስ አበባ ስታዲየም የተካሄደው የኢድ ጸሎት ስርአት ላይ ሁከት የቀሰቀሱ አክራሪ ዋሃቢ ሰለፊዎች ላይ የተወሰደውን አድማ የመበተን እርምጃ "የኃይል እርምጃ" ሲል አውግዞታል፡፡ ልብ በሉ የጸሎት ስርኣት በሚካሄድበት አካባቢ የራስን አመለካከት በማሰተጋባት ጫና ለማሳደር ዓላማ ሰላማዊ ሰልፍና ሕዝባዊ ስብሰባ ማካሄድ ክልክል ነው፡፡ ክልከላው የተፈቀደ ሰላማዊ ሰልፍና ሕዝባዊ ስብሰባንም ያጠቃልላል፡፡

በዚህ የጸሎት ስርኣት ላይ "ኃይል አለን" ብለው በጀብደኝነት ሰላም በማደፍረስ የጸሎት ስርኣት ያወኩት የአክራሪው ቡድን ጀሌዎች ናቸው፡፡ ፖሊስ የጸሎት ስርአት በሚከናወንበት አካባቢ የዚህ አይነት ሁከት መቀሰቀስ የማይቻልና ሕገወጥ በመሆኑ፣ የዚህ አይነት ድርጊት በሚፈጽሙ ላይ እርምጃ እንደሚወስድ ቀደም ሲል በተደጋጋሚ አሳውቆ ነበር፡፡

በማንአለብኝነት በዕለቱ የጸሎት ስርአቱን ለማወክ በሞከሩ የአክራሪው ጀሌዎች ላይ ተመጣጣኝ እርምጃ ወስዷል፡፡ ፖሊስ የሰዎችን ሰላምና ጸጥታ የማስከበር በሕግ የተሰጠው ኃላፊነት የተጣለበት መሆኑም ሊታወስ ይገባል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሰፊው ሙስሊም ሕብረተሰብ የጸሎት ስርአቱ ላይ አንዳችም ረብሻ እንዳይፈጠር ሕግ የማስከበር ስራ እንዲሰራ ለመንግስት ጥሪ አሰተላልፏል፡፡

ፖሊስ እርምጃውን የወሰደው በዚህ አግባብ ነው፡፡ የአዋኪዎቹን አድማ ለመበተን አንድም የጦር መሳርያ የታጠቀ የፖሊስ ሰራዊት አባል አልነበረም፡፡ አደማ በታች ኃይል ቆመጥ የታጠቀ ነበር፡፡ አድማ በመበተኑ ሂደት ላይ አንድም የጥይት ድምጽ አልተሰማም፡፡ በአንድም አዋኪ ላይ የከፋ ጉዳት አልደረሰም፡፡ ይህ ተገቢና ተመጣጣኝ ሕግ የማስከበር እርምጃ እንጂ የሃይል እርምጃ አይደለም፡፡

አንድነት ከፍተኛ ቁጥር ያለውን ሙስሊም ሰላምና ጸጥታ ለማስከበር ለተወሰደው እርምጃ ያልሆነ ትርጉም ለማሰጠት "የኃይል እርምጃ" ከማለትም አልፎ ግድያ የተፈጸመ ሁሉ ለማስመሰል ሞክሯል፡፡ እውነቱን ለመናገር አበአድማ በታኙ ኃይል የአንድም ሰው ሕይወት አልጠፋም፡፡ አንድነት የህገወጥ ግድያ አሳስቦት ቢሆን ኖሮ አክራሪዎቹ ሼህ ኑሩ ይማም ላይ የፈጸሙትን አሰቃቂ ግደያ አውግዞ መግለጫ ባወጣ ነበር፡፡ ይህን አላደረገም፡፡

የአክራሪው ቡድን ዓላማ ይወቃል፡፡ የአመለካከት የበላይነት ጥያቄ ነው ያለው፡፡ የአመለካካት የበላይነት ጥያቄ የስልጣን ጥያቄ ነው፡፡ የስልጣን ጥያቄ ደግሞ ግልጽ የፖለቲካ ጥያቄ ነው፡፡ የአክራሪው ቡድን የአመለካካት የበላይነት እንቅሰቃሴ የሚመራው በውጭ ኃይሎች ነው፡፡

የዋሃቢ ሰለፊ አስተምህሮ የበላይነትን የሚያራምድ እንቅስቃሴ ከ1960ዎቹ ጀምሮ  ሙስሊሞች በሚኖሩባቸው የተለያዩ ሃገራት ሲካሄደ መቆየቱ ይታወቃል፡፡ እንቅስቃሴዎቹ ከተካሄደባቸው አገራት መሃከለ  ህንድ ካሽሚር ግዛት፣ ፓኪስታን ፣ አፍጋኒስታን፣ ሩሲያ ቼቺኒያ፣ ማሊ፣ ሱዳን፣ ግብጽ ተጠቃሽ ናቸው፡፡ በለፉት ሁለት አስርት አመታት ብቻ ለዚህ የሰለፊ ዋሃቢ አክራሪነትን ለማስፋፋት እንቅስቃሴ ከሳኡዲ አረቢያ ብቻ ወደ 87 ቢሊየን ዶላር ገንዘብ ወጪ ተደርጓል፡፡

እንግዲህ አንድነት ፓረቲ በስልጣን ላይ ባለው ፓርቲና ሕገመንግስታዊ ስርአቱ ላይ ባለው ጭፍን ጥላቻ እየተመራ ስርአቱን ሊንድ ይችላል ያለውን ሁሉ ሲያነፈንፍ ዘንድሮ እነሆ በውጭ ኃይል የሚደገፉ የዋሃቢ ሰለፊ አክራሪዎች ላይ ወድቋል፡፡ አንድነት በጭፍን ጥላቻ ታወሮ ሲደናበር እጅግ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ሙስሊም ኢትዮጵያዊያንና ሌሎች ሰላም ወዳድ ዜጎች አክራሪውን ቡድን የሚጸየፉና እምርረው የሚቃወሙ መሆኑን እንኳን ዘንግቶታል፡፡በዚህ አካሄዱ  የአክራሪውን ድጋፍ አገኛለሁ በሎ ከአብላጫው የኢትዮጵያ ህዝብ ጋርም ተጋጭቷል፡፡

ሰማያዊ ፓርቲ ያወጣው መግለጫ የተለያየ ሰው ስለጻፈው አቀራረቡ ተለየ እንጂ በይዘት ደረጃ ከአንድነት መግለጫ ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ ስለዚህ መገለጫውን ሙሉ በሙሉ መመልከት አሰፈላጊ አይደለም፡፡ ይሁን እንጂ አንድ በመግለጫው ላይ የጠቀሰውን ሃሳብ ማንሳት አወዳለሁ፡፡ ይህም "መንግስት ከእስልምና እምነት ተከታዮች ጋር በፈጠረው ችግር ባለፈው አንድ አመት ተኩል ብዙ ችግሮች ተፈጥረዋል፣ ሓብትና እውቀት የሚያድግበት ግዜ ባክኗል፣ በሰው አካልና ንብረት ላይ ጉዳት ደርሷል፣ ሕይወት ጠፍቷል" የሚለው ነው፡፡

እዚህ ላይ ሰማያዊ ፓርቲ አቋምና ፖሊሲውን ሳይሆን ሰማያዊ የሚለውን ስሙን ሰላማዊ ሰልፍ ወጥተው ያሚሟቁለትን አክራሪዎች ውለታ ለመመለስ መንግስትን ችግር ፈጣሪ  አድርጎ

አቅርቧል፡፡ በመሰረቱ ችግሩን የፈጠረው መንግስት አይደለም፡፡ ችግሩ ወደመንግስት የሄደው ስርቻ ውስጥ ከተፈጠረ በኋላ ነው፡፡ የችግሩ ፈጣሪዎች ሙስሊም ኢትዮጵያዊያን አይደሉም፡፡ ችግር ፈጣሪዎቹ በአዲስ አበባ በአወሊያ መስጊድ የተሰባሰቡ በጣት የሚቆጠሩ ራሳቸውን የሙስሊሙ ተወካይ ብለው የሰየሙ ግለሰቦች፣ በደሴ የሃረከቱል ሸባብል ፊ ቢላል ሂጅራይተን የተባለው የጀሃድ ቡድን ግልገሎች፣ በአርሲ ቡሳ ሰገል የተባለው የጀሃድ ቡድን ርዝራዦች፣ በጅማ ከጥቂት አመታት በፊት በክርስቲያን ኢትዮጵያዊያን ላይ አስከፊ ጭፍጨፋ የፈጸመው ካዋርጂያ የተባለው ቡድን ውርዴዎች ናቸው፡፡ ሰማያዊ ፓርቲ እነዚህን በችግር ፈጣሪነት ማንሳት አልወደደም፡፡ ምክንያቱም ሰልፍ ቢጠራ አሟሟቂዎቹ ናቸውና፡፡

ሰማያዊ ፓርቲ "ሃብት ሊፈጠርበት የሚችል ብዙ የስራ ግዜ ባክኗል" በሚል ያነሳው መሰረተ ቢስ ወሬ ነው፡፡ ይህን ጉዳይ ስራዬ በሎ የሚከታተለው ለዚሁ ዓላማ የተቋቋመ ሕግ አስከባሪ አካል እንጂ ሁሉም የመንግስት ተቋማት አይደሉም፡፡ የሰማያዊ ፓርቲ አመራሮች በአዲስ አበባና አቢስአበባ ጅቡቲ በመገንባት ላይ ያለውን የባቡር መስመር፣ ግዙፍ የኤሌትሪክ ኃይል ማመንጫዎችና ሌሎች ግዙፍ የመሰረተ ልማትና የኢንደስትሪ ግንባታዎች፣ የአርሶ አደሩን ምርታማነት በከፍተኛ መጠን ለማሳደግ የልማት ሰራተኞች የአርሶአደሩን እጅ ይዘው በአነስተኛ ማሳው ላይ በመስመር የማረስን አመራረት ባህሉ እንዲያደርግ ደፋ ቀና ሲሉ አላዩ ይሆን? በአክራሪው ቡድን ጫጫታ አንድም የባከነ የስራ ግዜ የለም፡፡ ብልማት ላይ ያስከተለው አንዳችም አሉታዊ ተጽእኖ የለም፡፡

እርግጥ የሰማያዊ ፓርቲ አመራሮች "የአክራሪዎቹ እንቅስቃሴ በሕገወጥ መንገድ ወደስልጣን ለመውጣት የሚያስችል አንዳች ነገር ይዞ ይመጣል" በሚል ግምት እሱኑ ሲያስቡ ነው የከረሙት፡፡ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሚበጅ አማራጭ ፖሊሲ የማዘጋጀት፣ ፖሲያቸውን ማስተዋወቅ ወዘተ የመሳሰሉ ስራዎችን ትተዋቸዋል፡፡ ስራቸው አክራሪዎችን ማበረታታት፣ ለሕገወጥ ድርጊታቸውና ዕቅዳቸው ድጋፍ መስጠት፣ ለተቃውሞ ሰልፍ እንዲወጡ ማድረግ ወዘተ ብቻ ነበር፡፡ ስለዚህ ስራ ኖሯቸው ከነበረ ጥቂት አክራሪዎች በፈጠሩት ችግር ግዜያቸውን ያባከኖት የሰማያዊ ፓረቲ አመራሮች ናቸው፤ ፓርቲው ከአቶ ይልቃል ውጪ አመራር ካለው፡፡

በአጠቃላይ በኢድ አል ፊጥር በኣል ላይ ሊቀሰቀስ ተሞክሮ የነበረው ሁከት በአሉን ለማክበር ከታደሙት ሙስሊሞች ጋር ሲነጻጸር እጅግ በጣም ጥቂቶች የተሳተፉበት መሆኑን ያጋለጠ ነው፡፡ በዚህ አጋጣሚ በየሳምንቱ አርብ በአንዋር ምስጊድ አልፎ አልፎ ደግሞ በበኒ መስጊድ ሲንጫጩ ብዙ ይመስሉ የነበሩት የአክራሪው ጀሌዎች እጅግ ጥቂቶች መሆናቸውን ሕዝብ ተረድቷል፡፡ አክራሪው ቡድን የትም የማይደርስ በሞት አፋፍ ላይ ሆኖ በቀቢጸ ተስፋ የሚንፈራገጥ መሆኑም

ተጋልጧል፡፡ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ሰላማዊዋዊ ሙስሊሞች ታላቀ የጸሎት ስርአት በመረበሽ ስውረ የፖለቲካ አጀንዳቸውን ለማራመድ በሞከሩ ወገኖች ላየ የተወሰደው እርምጃም ፍትሃዊ፣ ተገቢና ተመጣጣኝ ነው፡፡